# አዎ! እሱ ጋ ያመኛል!



4ኛ እትም

አ ድ ኀ ኖ ም   ም ት ኩ

2 0 1 6 ዓ.ም

Scanned with CamScanner

# ማበድ ይሻላል

አእምሮዋን ያማታል፤ ሃና ትባላለች። በኮሮኮንቹ፣ በአቋራጭ፣ በድልድዩ በኩል አልፋ ቤታችን ትመጣለች፤ ስትመጣ ሰዓት አትመርጥም። የአቅሜን ለማንም ሳልናገር እንድትድን ጥሬያለሁ፤ አልተሳካልኝም እንጂ። መዳኗ በእኔ እንዲሆን አልተመረጠም ወይም ከነጭራሹ እንድትድን አልተፈቀደም።

አንዳንድ ቀን መጥታ በሩን በኃይል ስታንኳኳ ልጄ ከእንቅልፉ ይባንናል። በር የሚከፍት ሲጠፋ በጓሮ ያለውን መስኮት በድንጋይ ስታንኳኳ መሰለኝ አራት ያህል ጊዜ ሰብራዋለች። በሃኒቾ አልናደድም፤ ይልቅ ይበልጥ ታሳዝነኛለች። ባለቤቴ ግን በእሷ ጉዳይ ሆደ ሰፊነቴ ይገርማታል።

አንድ ዕለት ከእኛ የተረፈ ምግብ ልትሰጣት ስትል ገላምጬ አዲስ ያልተነካካ ምግብ እንድትሰጣት ስነግራት፣ አገለማመጤ ከዚህ በፊት ያላየችው ዓይነት ስለነበር ቅሬታ ልቧ ውስጥ ለሳምንት ያህል ተቀርቅሮባት እንደነበር አስታውሳለሁ።

አንዳንዴ ትክ ብላ ስታየኝ "ሃኒቾ ደህና ነሽ?" ስላት አንገቷን በአዎንታ ትነቀንቃለች። አይኗ ያሳዝናል። አይኗ ሁሉ ነገሯን የሚናገርባት ፍጡር ናት፤ አይኗ ስሜቷን ማንጸባረቂያ መስታወቷ



Scanned with CamScanner

ነውና ሁሉን ከአይኗ አገኘዋለሁ። ሃኒቾን አይቻት ከራባት ቃል ባታወጣ እንኳ አውቃለሁ።

አንድም በልጅነቴ ረሃብን የታናሽ የወንድሜን ያህል በቅርበት ስለማውቀው የራበውን ሰው ትክ ብዬ ማየት አልችልም፤ አሳነብሳለሁ፤ ክፉ ትዝታዬን ይቀሰቅስብኛል። ክፉ ትውስታችንን የሚያስታውሰውን የአእምሮ ክፍል በሆነ ጥበብ ማደንዘዝ ቢቻለን ብዬ አንዳንዴ እመኛለሁ።

ሁለተኛ ሃኒቾን አውቃታለሁና መራቧን አይቻት ባውቅ አይገርምም።

መንገድ ሳገኛት አሊያም ቤታችን ስትመጣ

"ደህና ነህ እዩ"

"ደህና ነኝ"

"አንቺ እንዴት ነሽ?" ስላት ጭንቅላቷን ደህና ነኝ ለማለት ትነቀንቃለች፤ ከዛ ውጪ ሌላ ምንም አትልም።

ባለቤቴ ሰፈሩን፣ ቤታችንን ጠላችው። በእሷ ጉዳይ ከእኔ ጋ ተያይዞ የሚነዛው ወሬ አወካት፤ በሌሊት እየመጣች እዩ ምግብ ስጠኝ የምትለው፤ በር የሚከፍት ሲጠፋ በጆርባ መስኮት የምትሰብረው ነገር ታከታትና ባልተለመደ ሁኔታ ልትቀና ይቃጣት ጀመር። ባመመው የቀና ሰው ካመመው ሰው በምን ይሻላል እላለሁ በልቤ። ከሚስቴ ጋር በሃኒቾ ጉዳይ ተጎረባበጥን፤ በር በኃይል ስታንኳኳ የልጅን መበርገግ መልመድ አልቻልንም።

## ፲፫ ጠማማ ቀን ...

ድብርት እንደ ነጭናጫ ሕፃን ልጅ ሱሪዬን ይዞ ሙጭጭ ያለበትን ውሎ አሳልፌ ቤቴ ገባሁ። ልጄ ባለመተኛቱ መግባቴን እንዳየ አባ እያለ ደስታ ፊቱ ላይ ተጥለቀለቀ። አንድ ቀን እንደ ዘላለም በሆነበት የትግል መንደር ለመውደቅ ጥንጥ ቀርቶኝ እቤት ስደርስ አባ... አባ የሚለኝ የልጄ ቃል ነው እጅ የማያሰጠኝ። የልጄን ጉንጮቹን፣ ግንባሩን፣ አንገቱን፤ የሚስቴን ጉንጭ ስሜ እራት እንደማልበላ ለሚስቴ ነግሬ ወደ መኝታ ቤቴ ሳመራ ባለቤቴ ገጼን እያየች "ውሎ እንዴት ነበር?" ስትለኝ ማለት የቻልኩት አድካሚ ነበር ብቻ ነው።

David Darybyshire Bad Day በሚል ግጥሙ

It's seems on some days

The whole world is against you

You feel really down, in a haze

How long do have to feel blue

እንዲል... አንዳንድ ቀን ይደብራል። አውጥተን፣ አውርደን ያቀድነው ይከሽፋል፤ ተስፋ ያደረግነው ይዘምማል። ዕድለኛ ያልመሆን ስሜት ውስጣችን ይርመሰምሳል፤ ኋላ የመቅረት ስሜት ይላፋናል፤ በአጠቃላይ ዛሬ ጥሩ የሚባል ቀን አላሳለፍኩም።

ሹልክ ብዬ አልጋዬ ላይ ጋደም እንዳልኩ በስንት መገላበጥ እንቅልፍ ሸለብ እንዳደረገኝ፤ በሩ ከዚህ ቀደም ተደብድቦ ከሚያውቀው በላይ በኃይል ተደበደበ። ባንኜ፣ ተንደርድሬ ወጣሁ።

ሃኒቾ ነች፤ አመድማ፣ ግራ የገባው ፊት እንዳየሁ ፍንትው ብሎልኛል።

በሩን እንደከፈትኩት እያጉረጠረጥኩ ፊቴን አጠይፌ እ ...!

ምንድን ነው ሕይወቴን የምታከብጂው? እንዴ.......!!!! ካለ እኔስ ሰው አታውቂም? ሁለተኛ እዚህ ቤት እንዳትመጪ....... አልኳት። የሌባ ጣቴን ፊቷ ላይ ደቅኜ እያውለበለብኩባት... ተናግርያለሁ!! እንዳልኩ አስታውሳለሁ።

ትክ ብላ አይታኝ በዝግታ አጎነበሰች። ቀና ብላ አየችኝ፤ ቀና ብላ ስታየኝ አይኖቿ እንባ አርግዘው ነበር። ቀስ ብላ አንገቷን ወደ መሬት ቀብራ፣ መሬት መሬት እያየች በዝግታ ትንሽ ወደፊት እንደተራመደች እሳት ለብሼ ፊቴን አጨፍግጌ ባለቤቴ ከኋላዬ እንደቆመች ዞራ ተመለከተችን አይኗ ያረገዘውን እንባ እያፈሰሰ ነበር።

አስተያየቷ፣ እንባዋ፣ አዟዟሯ ቢያሳዝነኝም ማዘኔን ፊት ነስቼ ፊቴን አዞሬ ወደ ቤቴ ገባሁ። ቀጥታ ወደ አልጋዬ ሄጄ ተመልሼ ተንጋለልኩ። እንደቅድሙ ማሸለብ አልቻልኩም እንጂ። እንባዋ፣ አስተያየቷ፣ አጎነባበሷ አንጀቴን በላው። አንሶላ ውስጥ ገብቼ እንደበደለ ሳይሆን እንደተበደለ፤ እንደጮኸ ሳይሆን እንደተጮኸበት፤ እንዳባረረ ሳይሆን እንደተባረረ ሆኜ አለቀስኩ።

ሃኒቾ ለእኔ ምን እንደሆነች የነበረንን ቁርኝትም የሰፈሩ ሰው ሁሉ በደንብ ያውቃል። ሚስቴ ይሄን ስለምታውቅ ነው እንደልቧ የማትናገረው፤ ይሄን ስለምታውቅ ነው ሐዘኔታዬ ላይ ቅናት የሚጣባት።

ሃኒቾ ታሪኬ ናት። ዋናው ታሪኬ እሷ ጋ ነው ያለው። እጮኛሞቾች ነበርን። አንድ ሸበጥ ለሁለት አድርገናል፤ ቤተሰብ አብሮነታችንን ጠልቶ ሊለያየን ሞክሮ አልሳካ ብሎት ያውቃል፤ በከፋ ካያት ጋ ለእሷ ተቆርቁሬ ተጣልቼላት አውቃለሁ፤ ጎድሎብኝ ሰርቃ ሞልታልኛለች፤ ለምና ተቀብላ ሰጥታኝ ታውቃለች፤ ኪሴ ኪሷ፣ ኪሷ ኪሴ ነበር።

ከእሷ የበለጠ ችስታ ስለነበርኩ ከእኔ በላይ እሷ ለእኔ ሆናልኛለች። ከሁሉ ሰው በላይ ስለምወዳት መንሰፍሰፌን በኩራት ነበር በየአጋጣሚው የምለፍፈው። እሷ ጋ ስሆን ቁጥብነቴ በስሱ ይተናል፤ ፍላጎት እና ገጠመኜን ከሌላው በተለየ እተነፍሳለሁ።

ትዝብት እና ፍርሃቴን አጋራታለሁ፤ እሷ ጋ ሆኜ ስደሰት ፈንጠዝያዬ ማንም እንደሌለ ዓይነት ነበር። ገመናዬን ነግሬያታለሁ፤ ገመናዋን ነግራኛለች፤ ገበናችንን ተገላልጠናል፤ መተዋወቃችን ነው የሚያገማምተን። አንድ ዕለት አበሳጭታኝ ሁለተኛ አጠገቤ እንዳትደርሺ ስላት ፈገግ እያለች

"በኋላ ስታስሰኝ ትውላለህ"

"አታውቂኝም!!"

በእርግጥ እንዳለችው በቶሎ የዛኑ ቀን አላሰስኳትም፤ ከሁለት ቀን በላይ ግን መሻገር አልተቻለኝም፤ ትዕቢት ተናነቀኝ። ፍቅሬ ከትዕቢቴ ስለሚበልጥ አይኔን በጨው አጥቤ አገኘቻታለሁ፤ ፍቅራችን አይናችን ውስጥ ይጮህ ነበር። እሷን ባለማግኘቴ ምክንያት

ተጭኖኝ የነበረው ድብርት በነነ፤ ልትመጣ ስትል እንደመጣሁ መደበቅ አልተቻላትም።

ሃኒቾ ቶሎ ቶሎ ታኮርፍ ነበር፤ እኔ መኳረፍ ጭንቅ የሚለኝ ሰው ነኝ። መለማመጥ ስለማልወድ እንድታዋራኝ ቀልብ ገዝቶ ኩርፊያዋን ለማርገፍ ድራማ ፈጥሬ እተውናለሁ፤ ማኩረፏን ረስታ ቀልቧን ትሰጠኛለች፤ መቅደድ እንጀምራለን።

ደግሞ ትቀና ነበር፤ መቅናቷን በሁኔታዋ ነው የምትገልጸው፤ ትገባኛለች። ሳትጠይቀኝ የቀናችበት የመሰለኝን ጉዳይ አብራራላታለሁ፤ ቀስ ብላ ፍትት ትላለች፤ ፈገግ ስል "ምን ያስቃሃል?" ትላለች።

ሰውነቷን ለልፊያ እያዘጋጀች የበለጠ አፌን ከፍቼ ስስቅ ትላፋኛለች፤ እላፋታለሁ።

ስስ ነበረች። እሷ በቶሎ ስለምትከፋ እኔም በትንሽ እንዳልከፋባት ይደብረዋል የምትለውን ነገር ላለማድረግ ትጥራለች።

ትንሽ ነገር ይረብሻታል፤ ሲጨንቃት አቅፋታለሁ፤ እጄን ጸጉሯ ላይ እያንሸረሸርኩ ሁሉም ነገር ይስተካከላል፣ ከባድ አይደለም፤ ደግሞ አምላክ ይረዳናል እላታለሁ፤ እርጋታ ሲያጥለቀልቃት ይሰማኛል።

እንደምትወደኝ ሁኔታዋ ሁሉ፤ እንደምትታመን እንቅስቃሴዋ ሁሉ፤ ከእኔ ጋ መሆን እንደምትፈልግ ሁሉ ነገሯ ያሳብቅባት ነበር!!!

ከነበር በኋላ ምን አለ?



Scanned with CamScanner

ሃኒቾን የምወዳት በጠይም ቆንጆ ፊቷ አልነበረም፤ የተማረኩት በጥቁር ዞማ ጸጉሯም አልነበረም፤ ያሸነፈችኝ በየዋህነቷ ነው። ሃኒቾ ለመድመቅ አለመፍጨርጨሯ ነው። ተፈላጊነቷን ለማሳየት አትዳክርም፤ ያላትን ለማጉላት አትታከክም። ምንም የሌለውም ሰው እንደሚወደድ ያሳየችኝ ሃኒቾ ነበረች።

አንድ ቀን ስለ ውሎዋ ስትነግረኝ ትረካዋን ወደ ጎን ትቼ የተዘናፈለ ዞማ ጸጉሯ፣ እርጋታዋ፣ ወዛም ጠይም ፊቷ ላይ ተመስጬ ቆንጅዬ ልጅ እንደሆንሽ ታውቂያለሽ አይደል? ስላት

ዝም ብላ ፈገግ ብላ እያየችኝ ዝም ስትል

የምር አታውቂም?

"እመቤቴን አላውቅም" እመቤቴን ስትል አማማሏ፣ አይኗ ያሳዝናል

"ማልልኝ እስኪ ቆንጆ ነኝ ግን?"

እስቃለሁ። የዋህ ባትሆን ለቆንጆ ነሽ ማልልኝ ትል ነበር?

ሃኒቾ ማለት ይቺ ነበረች በቃ!!! እሷ እመቤቴን ካለች ስለማትዋሽ ሁሉም እንደዛ ነው የሚመስላት።

የሁሉም መለኪያ የልቡ እውነት እና እምነቱ አይደል?

ሃኒቾ ዘመዶቿ ጋ ከፍለሀገር ስትሄድ፣ ስትመጣ፤ እኔም ከፍለሀገር የእናቴ እህት ማሚቱ ጋ ስሄድ ስመጣ አብሮነታችን እየሳሳ እየሳሳ ሌላ መልመድ ጀመርን። ሳንቆሳሰል፣ መራር ቃል ሳንነጋገር ተራራቅን። አብሮነታችን ሳስቶ በሂደት ተለያየን። ከፍለሀገር ለብዙ

ጊዜ ኖሬ፣ ትዳር መስርቼ፣ ልጅ ኖሮኝ - ተወልጄ ባደግኩባት ከተማ ተመልሼ ያከራየሁትን የቤተሰቦቼን ቤት አስለቅቄ መኖር ጀመርኩ።

ሃኒቾ አግብታ እንደነበር ነገር ግን ከብዙ ንትርክ፤ ከስንት ታርቆ መጣላት በኋላ፤ ከብዙ የጓደኞች፣ የዘመዶች፣ የሽማግሌዎች እና የቤተሰብ ምክር እና ሽምግልና በኋላ አብሮ መሆን አልሆን ብሏቸው እንደተፋቱ፤ ተቆጪዋ፣ መካሪዋ፣ ተቆርቋሪዋ ታላቅ ወንድሟ ሙሉጌታ ሲነዳው የነበረው አነስተኛ መኪና ከከባድ መኪና ጋ ተጋጭቶ ሕይወቱ እንዳለፈ፤ እናቷ እማማ ፀሐይ ታመው አልጋ ላይ ብዙ ጊዜ እንደማቀቁ፤ ካለመሰልቸት ብቻዋን ታግላ ማትረፍ ባትችልም እንዳስታመመቻቸው ከአብሮ አደጎቻችን ሰማሁ።

ሃኒቾ በሂደት ራሷን ማግለል፣ ብቻዋን መሆን፣ ራሷን አለመጠበቅ፣ ሥራ አለመሥራት፣ ብቻዋን ማውራት፣ ሲያናግሯት ምላሽ አለመስጠት፣ የተዘበራረቀ ነገር ማውራት መጀመሯንም ከፍለሀገር እያለሁ ሰምቼ ነበር።

ለመጀመሪያ ጊዜ ስንገናኝ፤ "እዩ ደህና ነህ?" ብላ እቅፍ አደረገችኝ፤ እስተቃቀፏ እንኳን መጣህልኝ ዓይነት ነበር። እንዳቀፍኳት ደህና ነኝ አንቺ ደህና ነሽ ስላት እንዳቀፈችኝ ቃል ሳታወጣ አንገቷን ነቀነቀች፤ የሆነችውን ሁሉ ብሰማም ባይኔ ስመለከታት ሰውነቴ ብርክ ያዘው...

ያቺ ፍንጣሪ ነጥብ የምታህል ቆሻሻ ልብሷ ላይ ሲያርፍ ደስ የማትሰኝ፣ ጽዳት፣ ማጠብ፣ ማስተካከል ዋነኛ መለያዋ የነበረው ሃኒቾ ውሃ አይቷት የማያውቅ፣ የተረሳ፣ ሽበት ጣል ጣል ያለበት ጸጉር፤



Scanned with CamScanner

ጉስቁል፣ ጥቁር ከስት ያለ ፊት፣ የመነቸከ ሽሮ ቀለም ቲሸርት፣ ብዙ እድፍ የተሸከመ ቀለሙ ይሄ ነው የማይባል ሰፊ ሱሪ ለብሳ ባዶ እግሯን አጠገቤ ስትቆም፣ ስታቅፈኝ ከአጠገቤ ዞር እስከትል እንኳን እንባዬን መቆጣጠር አልቻልኩም። ሁኔታዋ፣ ያሳለፍነው ትናንታችን፣ ሳቃችን፣ ገመናችን፣ መተሳሰባችን ሁሉ አንድ በአንድ ቅልብጭ ብሎ ታወሰኝ። ሕይወት እስኪያስጠላኝ ድረስ ተደበትኩ... ሰው የመሆን ከንቱነቱ ተዳሰሰኝ!! አንዳንድ ስሜት እውነት ካልዳሰስነው አናውቀውም!!

አብሪያት መቆም ስላልቻልኩ ቻው እንገናኛለን ብዬ ጥያት ሄድኩ። አልሆነልኝም እንጂ የዚያን ሰሞን እንድትድን ያልገባሁበት አልነበረም።

በቀን ብዛት ሰውነቴ ለመዳት እና ሲያያት ማመጽም አቆመ።

ሃኒቾ ከሌሎችም ጋ በጣም ትንሽ ብታወራም፤ ከእኔ ጋ ሲሆን እንደበቷ አይታዘዝላትም መሰለኝ

"እዩ ምግብ ስጠኝ"

"እዩ ሳንቲም ስጠኝ"

"እዩ ደህና ነህ" በቀር ሌላ ቃል አትሰነዝረም።

ሃኒቾ አልፎ አልፎ ደህና ነህ ለማለት ብቻ፣ ወይም ሳንቲም ስጠኝ ለማለት ብቻ፣ ምግብ ስጠኝ ለማለት ብቻ ቤታችን ትመጣለች። ደህና ነህ ለማለት የመጣች ቀን ገንዘብም ምግብም

ብሰጣት እሽ አትልም። በር ስታንኳኳ ከእኔ በቀር ማንም ይከፈት ማንም እዩ አለ?

የመጀመሪያ ጥያቄዋ ነው።

ችግሩ በር ስታንኳኳ በኃይል ነው። እንኳን ሕፃን ልጅ ትልቅ ሰው ያስበረግጋል። በስንት መከራ ተባብሎ የተኛውን ልጄን በር በኃይል እያንኳኳች ታባንነዋለች። ቀስ ብለሽ አንኳኪ ብለን እኔም ሆነ ሚስቴ ያልገሰጽናት ጊዜ አልነበረም፤ ለግሰጻችን ምላሿ ፈቷን አመስክና ቅልስልስ እያለች በአይኗ መለመን ብቻ ነው።

ሚስቴ እሷ ስትመጣ ፈገግታዋ ይደበዝዛል።

ሰዓት እላፊ እየመጣች፤ በስንት አሹሩሩ የተኛውን ልጃችንን እያባነነች፤ ባለመኖራችን የበሩን ድብደባ ሰሚ ስታጣ የመስኮት መስታወት እየሰበረች አስመረረችን።

ያ ዱካካም ቀን ለእሷ የነበረኝን ሐዘኔታ አትንኖት እያጉረጠረጥኩ፣ የመጣልኝን እየለደፍኩ ሁለተኛ እንዳትመጪ አልኳት።

ሄደች።

ሃኒቾ የድሮው እዮብ በልቧ ስላልጠፋ፣ ተካፍለን የበላናት፣ ተበድረን የተካፈልናት፣ የሳቅነው፣ የተጨቃጨቅነው ከውስጧ ስላልጠፋ ልቧን የወጋሁት ያህል ማንባረቋ ያሳመማት ይመስለኛል። ሁሉም እንደሚያባርራት አባረርኳት፤ ሁሉም እንደሚማረርባት ተማረርኩባት።



Scanned with CamScanner

ሃኒቾ ከቤቴ ቀረች።

መንገድ ላይ ሳገኛት አንገቷን ደፍታ ታልፈኛለች።

በስሜት ተገፍተን የበደልነው ሰው አንገቱን ሲደፋ ከማየት በላይ ያለ ሕመም የትኛው ነው?

ከፋቴን ሁለመናዋ ላይ ተነቅሳው የምትዞር መሰለኝ። ከፉ እንደሆንን የሚመሰክሩብን ተንቀሳቃሽ ሥጋ ለባሽ፣ ተጨባጭ ምስክሮች እንደማየት ያለ ጥፋተኛ ስሜትን በገላችን ውስጥ የሚረጭ ሌላ ምን ዓይነት ክስተት ይኖር ይሆን?

ለግንቦት ልደታ ዕለት የሰፈር ልጆች አብዲ ሱቅ ጎን ያለችው ሜዳ ጋ ተሰብስበው ቡና አስፈልተው በስፒከር ሙዚቃ እያጫወቱ፣ እየጠጡ፣ እየተተራረቡ ሲዝናኑ ሃኒቾ ከሙዚቃውም ከቡናውም ትንሽ ነጠል ብላ ብቻዋን ጽዱ ሥር ለመቀመጫነት ከተቀመጠ ድንጋይ ላይ አይኗን ቡዝዝ አድርጋ ተቀምጣ ሳለች ቀስ እያልኩ አጠገቧ ደርሼ ሃኒቾዬ አልኳት። ሰማይ ላይ ቡዝዝ አድርጋ የተከለችውን አይኗን ወደ እኔ ስታዞር ሃኒቾ አጥፍቻለሁ ይቅርታ አድርጊልኝ ብዬ በአይኔም ጭምር ለመንኳት። ሌላ ተጨማሪ ነውር ላለመስማት ይሆን አላውቅም ብቻ የደበዘዘ ትዝብት ለበስ ደረቅ ፈገግታ አሳይታኝ በእርጋታ ተነስታ ሄደች።

ብዙ ሰው ሲያባርራት፣ በር ሲዘጋባት፣ ውሃ ሲደፋባት፣ ሰላም ስትላቸው ሲዘጓት ምንም ያልመሰላት ልጅ የእኔ ሲሆን እንደዋዛ አልተወቸውም። ምን አለ ብትሰድበኝ፤ ምን አለ ከአጠገቤ ሂድ ብላ ድንጋይ ለማንሳት ብትሞክር፤ ምን አለ ከፉ ቃል ተናግራ የሠራሁትን

ብልግና ብታፈዘው፤ እሷ ጠቢብ ናት፣ ጠላቷን የምትበቀለው ከእብድ በማይጠበቅ ዝምታዋ ነው!!

ዝምታን የመሰለ መሣርያ አልባ መቅጫ ምን አለ?

የሆነ ቀን ጠጥታ፤ የሆነ ቀን እርቧት፤ የሆነ ቀን ልትሰድበኝ፤ የሆነ ቀን ሳንቲም ፈልጋ የምትመጣ መስሎኝ ጠበቅኋት። በራችን በኃይል ሲንኳኳ እሷ እየመሰለችኝ ስሮጥ በሩን እየከፈትኩ ጠበቅኋት። ደህና ነሽ ሃኒቾ ስላት አንገቷን ወደ ላይ እየነቀነቀች ደህና ነኝ እንድትለኝ፤ ሳገኛት አንገቷን እንዳትደፋ ጠበቅኋት፤ ካለ ቀጠሮ መጠበቅ እናዋዥ ነውና አናወዘኝ።

ዳግመኛ ለማናገር፣ ይቅርታ ለመጠየቅ ፊቷ መቆም ብፈልግም ፈራኋት። ሳያት የሆነ ሰው በደሌን ተነቅሶ፣ ነውሬን የሚለፍፍ ዓይነት ድብርት ይዳበለኛል። በቀን ብዛት ይሄ ስሜት ድል ይነሳል ብልም አልሆነም። ሁሌም ሳያት የሚሰማኝ ስሜት ትኩስ ድብርት ነው። እኔ ከሚሰማኝ ስሜት እሷን ስበድላት የተሰማት እና ከሚሰማት አይበልጥም ብዬ መደበቴን ታገልኩት። አንዳንድ ቀን ያበድኩት እኔ የበደለችኝ እሷ ብትሆን እያልኩ እስከመኝ ድረስ እረፍት አጣሁ። ትግሌ ከአቅሜ በላይ ሲሆን ከሃኒቾ ጋር የነበረኝን ትዝታ፣ የበደልኳትን በደል፣ ፊት መንሳቷን፣ ለማምለጥ እሷም ትዝታዋም አይደርሱበትም ብዬ ወዳሰብኩት ቦታ ለሚስቴ አሳማኝ የሚመስል ሰበብ ደርድሬ ቤታችንን አከራይተን ያን ሰፈር ለቀን ሄድን።

በሽሽት የበዳይነት ሕመሜን ድል አደረገው ከሆነ አየዋለሁ!



Scanned with CamScanner

# ውርስ ሕይወት

አባቴ ለብዙ ዓመታት ታስሮ ነበር። አስራ አራት ዓመቴ አካባቢ ተፈታ፤ የተወለድኩት ያን ጊዜ ነበር ማለት ይቻላል፤ አባቴ ሲፈታ እኔም ተፈታሁ። አባቴ አስራ አራት ዓመት ድረስ ሳስብ የነበረውን ቀስ እያደረገ ዳመጠው።

አባቴ የላላ፣ የተቆጠበ ማኅበራዊ ግንኙነት ያለው፣ ረጋ፣ ጀንተል፣ ኮስተር ያለ ግለሰብ ነው። ብዙ ሰዓት ዝም ይላል፤ የስሜት መለዋወጥ አይታይበትም፤ ጺሙ በብዙ ሲያድግ በመቀስ በትንሹ ይከረክመዋል፤ ልብሶቹ፣ የሚጠቀምባቸው እቃዎች ስትር ያሉ ናቸው።

ከእስር እንደተፈታ እኖር ከነበረበት ከእናቴ ቤተሰቦች ቤት ወስዶ ተከራይቶ ከነበረው ሰፊ ግቢ ውስጥ መኖር ጀመርን።

ቤታችን ቅዝቅዝ ያለ ነው። ቅዝቅዝ ያለው ብዙ ወንድም እና እህት ስለሌለን ነው ወይስ እናት ስለሌለኝ ነው፣ አልያም ደግሞ አባቴ ከሰው ጋ በደማቁ ስለማይግባባ፤ ምክንያቱን እርግጠኛ ባልሆንም ውጤቱ ግን ቀዝቃዛ ሰፊ ትልቅ ግቢ ውስጥ ነው የኖርነው።

መቀዝቀዙ የገባኝ፣ በየአገጣሚ የትምርት ቤት ጓደኞቼ ጋ ቤታቸው ስሄድ ይሳሳቃሉ፣ ይጨቃጨቃሉ፣ ይካሰሳሉ፤ በዚህም አቀና ነበር። እጦታችን ያወቅነው ዕለት ጉድለት ይሰማን የለ?!



Scanned with CamScanner

ስሜ ዋሲሁን ቢሆንም አባቴ ዋሴ ነው የሚለኝ፤ ምንም ነገር ሲያስደርገኝ ሆነ ሳደርግ አምኜበት እንዲሆን አድርጎ ሠርቶኛል። ከፍቶኝ ለምቦጬን ከዘረገፍኩ "ዋሴ ማኩረፍ የአቅመቢስነት ማሳያ ነው፤ መጀመርያ የከፋህን፣ ቅር ያለህን በእርጋታ አስረዳ" እያለ የውይይት ባሕል ልቤ ውስጥ እያኖረ ነው ያሳደገኝ።

ያምንብኛል። እንደመታመን አበርቺ እጽ እንደሌለ ያወቅኩት ለራሴ ያለኝ በጎ እና የእችላለሁ ወኔ ከብዙ አቻዎቼ መለየቱን እና ምንጩን ስረዳ እና ሲገባኝ ነው።

በጨዋታ መሀል

"ይሄውልህ ዋሴ ሁልጊዜ እሮሮ የሚዘበዝቡ፣ ሁልጊዜ ሰው ማጣጣል ላይ የተመሰጡ ሰዎች፣ ሁልጊዜም አልተሳካልን ዓይነት ደረት የሚመቱ፤ ለውድቀታቸው ሰው የሚወቅሱ ሰዎች፣ ለመውደቃቸው ኃላፊነት ከማይወስዱ ጋ አትወዳጅ" ይላል።

ይሄ ሰውዬ ጓደኛ የሌለው ለውድቀታቸው ኃላፊነት የሚወስዱ አጥቶ ይሆን እላለሁ አንዳንዴ።

ደግሞ በሌላ ቀን እጅግ ብዙ ቆይቶ

"ዋሴ" ይላል። ልገልጸው የማልችለው አጠራር አለው። ሁሉም ሰው ዋሴ ብሎ ቢጠራኝም በእሱ ዓይነት መንገድ የሚጠራኝ ሰው አልገጠመኝም። የሆነ አለኝታዬ ዋስትናዬ የሚለኝ ነው የሚመስለኝ፤ እወድሃለሁ የሚለኝ በአጠራሩ ውስጥ ባለው ድምጸት በኩል ነው።

"ይሄውልህ ዋሴ ሰው አንተ ላይ ስለሚይዘው አቋም እንዳትጨነቅ፤ ሰው ለማስደሰት ከዳከርክ የራስህ እውነት ሳይኖርህ ታልፋለህ" ይላል።

አባቴ ጥንቅቅ ያለ ሰውዬ ነው፤ ነፍስ እያወቅኩ ስሄድ ነው ለእሱ ያለኝ ፍቅር እና አክብሮት ያየለው።

ብዙ ዝም ስለሚል ሲያወራ ተስገብግቤ ነው የምሰማው፤ እጦትን የመሰለ ነገሮችን ተፈላጊ አድራጊ ያለ አይመስለኝም እኮ።

"ይሄውልህ ዋሴ"

ወዬ አባቴ

"ስንት ዓመት መቀመቅ ያወረደኝ ሐቀኝነቴ ነው፤ ኃላፊነቴን በአግባቡ ለመወጣት ስዳክር፤ ብልሹ ካልኩት አሠራር ጋ ስታገል፤ መደለያቸውን በጄ ስላላልኩ መቀመቅ ውስጥ ወረወሩኝ።

ብቻዬን ቆምኩ!

በእርግጥ እኔ ቆምኩ ልበል እንጂ ለብዙ ሰው ወድቄያለሁ፤ የወደቀ ከሚለው ጋ ማበር የሚፈልግ ማን አለ? ወደቀ ብለው ተዘባበቱብኝ፤ ስንት ዓመት ለመኖር ነው ግን እንዲህ የከፋት እላለሁ፤ ስለ ተቻለ ብቻ አሳማም ጅብም እንዴት ይኮናል?!

ይኸውልህ ዋሴ

ለእራስህ እውነተኛን መሆን የመሰለ የሕሊና እረፍት የለም፤ ከራስ ጋ ሰላም ከመሆን በላይ ምን ሽልማት አለ? ወድቋል ብለው



Scanned with CamScanner

ሲዘባበቱ እኔ ያልሠራሁት መጥፎ ተግባር ምቹ ትራስ ሆኖኝ ከሰላሜ ጋ ነበርኩ።

አንተ እንዲህ የምትወደኝ እኮ፣ አንተ እንዲህ የጎበዝከልኝ'ኮ ለእውነቴ የተሰጠኝ ሽልማት ነው፤ በዚህ ዕድሜ ጤነኛ የሆንኩት እኮ አምላክ ለመታመኔ የሰጠኝ ስጦታ ነው፤ ሰው ሽልማት ጥሬ ገንዘብ ብቻ ይመስለዋል" ይል'ና በስሱ እንደሁሌው ጥርሱን ገለጥ አድርጎ ፈገግ ይላል፤ አሳሳቁ ሞገስ አለው!!

"እኔን ያሳቀሉኝ እኮ በእስተርጅና የሚመታቸው ልጅ፣ የማይወዳቸው ልጅ ኖሯቸዋል፤ ያመኑት ከዷቸዋል።

"እግዚሃር በሚደግሱት ዝክር የሚሸወድ መስሏቸዋል" እያለ አፉን በትንሹ ከፍቶ ጥርሱን እያሳየኝ ፈገግ ይላል።

አባቴ የሚለኝን ሁሉ እየሆነ ያሳየኝ መምህሬ ነው።

"ይኸውልህ ዋሴ ጥቃቅን ነገር ላይ አታተኩር፤ የምትኖርለት መርሕ ይኑርህ፤ አመቀመቅ ድረስ የምትሄድለት ሕልም እና መርሕ ይኑርህ።"

የሚኖርን እውነት ከመስማት በላይ ምን ሐሴት አለ??

ብቻዬን መቆም አስተምሮኝ፣ ጥቂት ቀን ታሞ ጥቂት ቀን አስታምሜው አለፈ። ብዙ ቆይቼ እስር ቤት ሳለ የጻፋቸውን ሐሳቦችን እና ገጠመኞቹን ሳነብ ከዕድሜዬ በላይ አበሰለኝ።

ሕይወቱ ላይ የብስለቱ ዳና ያረፈብኝ የአባቱ ልጅ እኔ ዋሴ ነኝ!!!

ገጽ ፩

# እውነት እንደ ገጹ

የተሸነፈ ሰው ምንም ታሪክ ያለው አይመስላቸውም። የሚሰማ ታሪክ ያለው ድል ላይ ብቻ ይመስላቸዋል!! ጣፋጭ የፍቅር ሕይወት ያለው ሰልካካ፣ አይነግቡ ፊት ብቻ ነው የሚመስላቸው። ስንት ፉንጋ አይን ውስጥ የማትገባ ጣፋጭ ትዝታ እንዳላት መጠርጠር ለምንድን ነው የሚሳናቸው?

ካደኝ ስላቸው በውስጣቸው 'ድሮም እኮ' የሚል መልእክት ፊታቸው ላይ አያለሁ። በተለይ ቁመናውን፣ ሰፊ ደረቱን፣ ፈገግታውን በአካል ወይም በፎቶ የሚያውቁት ሰዎች የሚለኩን በቁመና እና በፊታችን ቅርፅ ነው። ፊት፣ ቁመና እና ደምግባት ለመተዋወቅ ብቻ የሚረዳ አይመስላቸውም። ከተዋወቅን በኋላ የጤነኛ ሰው መመዘኛው ማንነት እንደሆነ አይገባቸውም።

ለምኖኝ ነው የተወዳጀነው!

ልበ-ሙሉነትን እኔ እንዳስተማርኩት ብነግረው ማን ያምናል? ወዳጆቻችን ሲቀላቀሉን ደቂቃዎች ሳይቆጥሩ ነው የእኔን ይሁንታ እየተማጸኑ የሚለፍፉት። ጭንቅላቱን ገንቢ ነገር በየቀኑ እየመገብኩ፣ ሥራውን፣ ውሎውን እና የትምህርት ደረጃውን እኔ ነኝ አሰበጣጥሬ ወደ ስኬት ያንደረደርኩት። ምን ያደርጋል? እኔው ላይ ተንጠልጥሎ

ባለ ሕልም ካደረግኩት በኋላ ረገጠኝ፤ ሕልምን እውን አድርጎ መኖርያ ትርጉም ከመስጠት በላይ ምን አለ?

ድሮ የሚያውቁት ሰዎች እስኪጠፋባቸው ነው ሞገሳም ያደረግኩት። ውሸት አይደለም፤ እሱም 'ከስሜ በቀር ማንነቴን አድቦልቡለሽ ነው ያበጃጀሽኝ' ይላል።

ያልቀረቡን፣ ከሩቅ የሚያቁን እንዴት አድርጋ ብትሰጠው ነው እንደዚህ ዓይነት መልከመልካም እና ስኬታማ ሰው እዚች አስቀያሚ ጋ የተለጠፈው ይሉት ነበር። ጫጫታው ሲደጋገም ሰማቸው። ሳያማክረኝ የማይራመደው፣ ሳልሰማ የሚያጸድቀው ነገር አልነበረም፤ እሱ ለእኔ ኃላፊነቴ ነው።

እሱ ግን ካደኝ።

ዓለም ከጀርባ ላለው እውነት ትኩረት አትሰጥም፤ የእሱ መብራት ምንጩ እኔ እንደነበርኩ ማን ያውቃል!?

እሱ ራሱ ብርሃኑ ሲያሸበሽብለት እንዲያበራ የሆንኩለትን ዘነጋው፤ አድናቆት አወከው፣ የገዘፈ ሲመስለው አነስኩበት።

ጭብጨባ አስተውሎቱን የማይነጥቅበት የተባረከ ነው!

አስተውሎት የሌለበት ከፍታ ይዋል ይደር እንጂ ውደቀት መጠናቀቅያው እንደሆነ ነግሬው ነበር። ትምክሕቱ ሲጎላ አታስፈልጊኝም፣ ብቻዬን ሙሉ ነኝ ዓይነት እንቅስቃሴ ላይ እንደነበረ አስተውያለሁ። አንድ ቀን ከወዳጆቹ ጋ ቢዝነስ ለመሥራት ሲንቀሳቀስ 'ውል አብጁ' አልኩት።



Scanned with CamScanner

"ማርያማዊት ሕግ ላይ ሙጭጭ አትበይ፤ ዓለም በሎጂክ አትመራም፤ በፍቅር፣ በመግባባት እንጂ" አለኝ።

እንኳን ቢዝነስ ወዳጅነትም ራሱ ያልተጻፈ ሕግ አለው። ሁሉም ግንኙነት እኮ ሳታወራ የምትግባባበት መርሕ አለው፤ በአምነዋለሁ፣ በወንድሜ ነው፣ እሱ ማለት ተብሎ ውል አልባ ቢዝነስ መጨረሻ ካተረፍነው የበለጠ ነው የሚያከስረን።

ትኩር ብሎ አይቶኝ "አልገባሽም! አልገባሽም! አሁን ራሱ ያወራሽው ሎጂክ ነው! እግዜር ስላለመኖሩ ኢ-አማኝ በጸበል ለዳነ ሰው ቢዘበዝብለት የሚያምነው ይመስልሻል? ጸበልተኛው መርቻ እንደበት ባይኖረው እንኳን"

ዘበዘብሽ እያልከኝ ነው? ደግሞስ ምኑን ከምኑ ለውሰኸው ነው ሰማያዊ ሕይወትን ከዓለማዊ የሥራ ግንኙነት ጋ የዶልከው?

"እንደሱ አላልኩም!"

በሂደት መለሳለሱን እየተወ ከእኔ መቃረንን እውቀት አረገው። ለእሱ ስል እንደምሞግተው ትዕቢቱ ሸፈነበት። ሰው የሚመዘነው በአድራጎቱ ውስጣዊ ፍላጎቱን [1] በመመርመር እና በመረዳት አይደለምን?

የምናደርገው እና የምንናገረው በደረቁ ከተተረጎመ ማን ከማን ጋ ይኖራል!?

ፈርጠም እያለ መጣ።

[1] Intention

የሆንኩለትን ዘነጋ፤ ለስኬቱ የከፈልኩለትን ዋጋ አደበዘዘው፤ እንቅስቃሴውን ይደብቀኝ ጀመር፤ ውጤቱን ያውም ያሳካውን ነው የሚነግረኝ፤ ያቀደውን ሳይሆን የወሰነውን ነው የሚያሳውቀኝ።

አንድ ቅዳሜ ዕለት ቤቱ ሄጄ ተጨዋውተን እየተመካከርን ሳለ ድንገት አንገቴን እየሳመ፤ እያቻኮለ የለበስኩትን ከላዩ ገፈፈው። ቤብ 'what's wrong' ከማለት ውጪ መናገር አልቻልኩም፤ ከሌላ ቀኑ በተለየ ተዋሰብን። ሴቶች አዲስ ነገር ስለምንወድ ይሁን፣ በተለየ መንገድ እርካታ ስለተሰማኝ ይሁን፤ እንደሚወደኝ ስለነገረኝ፤ ባልጠበቅኩበት መንገድ ስለተኛኝ ይሁን ብቻ ደስስ ቢለኝም ውስጤ ትንሽ ጥርጣሬ ተወለደች። የተሰማኝን ደስታ ከጥርጣርዬ ጋ ተደበላልቆ ምንም ሳልነግረው ግርታ ፊቴ ላይ እየታየ ተለያየን።

በሂደት... ማግኘት፣ ናፈቅሽኝ ማለት፣ ሴት ልጅ ከወንድ ልጅ መስማት የምትፈልገውን መስጠት ነሳኝ። ይጠፋብኛል፣ አያገኝኝም፣ ሲያገኘኝ ያጣጥለኛል፤ ድክመት፣ እንከኔን ያስሳል።

ትናንትን መርሳት፣ የተዋለለትን መዘንጋት የደካማ ባሕሪ ነው!! ደካማነት ምቹ ስፍራ ሲያገኝ እና ጊዜ ሲደላደልለት የሚያብብ ደዌ ነው፤ ከአንደበቱ ቃል ሳያወጣ በሁኔታው ብቻ አባረረኝ፤ ሁኔታ የድርጊት ዋዜማ ነውና ሂጂ ሳይለኝ ሁኔታውን ስማሁት። ትዝታው ይበቃኛል ሄድኩለት ...